# የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ

## በተከለሉ የወጪ፣ ገቢ፣ ጅምላ እና ችርቻሮ ንግድ ስራዎች የውጭ ባለሀብቶች ኢንቨስትመንት ተሳትፎ አፈፃፀም

## መመሪያ ቁጥር ፲፱፩/፳፻፲፮

መጋቢት ፳፻፲፮ ዓ.ም

አዲስ አበባ

## የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ
## በተከለሉ የወጪ፣ ገቢ፣ ጅምላ እና ችርቻሮ ንግድ ስራዎች የውጭ ባለሀብቶች ኢንቨስትመንት ተሳትፎ አፈፃፀም
## መመሪያ ቁጥር ፲፪፩/፳፻፲፮

በኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር 474/2012 መሰረት ውስን የንግድ ዘርፎችን ከውጭ ኢንቨስትመንት ውድድር በመከለል የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን በብዛት እና በጥራት ለማፍራት፤ ከአለም-አቀፉ የንግድ ትሥሥር ስርአት ጋር ይበልጥ እንዲተዋወቁ ለማስቻል፤ በሂደትም እሴትን ወደሚጨምሩ የኢንቨስትመንት መስኮች እንዲሸጋገሩ በማድረግ በአገር ውስጥ አቅሞች ላይ የተመሠረተ ዘላቂ ሀገራዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችል ፖሊሲ ተግባራዊ ሲደረግ የቆየ መሆኑን በመገንዘብ፤

በፖሊሲው አፈፃፀም ውስን ውጤቶች ቢመዘገቡም ይህ አሰራር ተግባራዊ ማድረግ ከተጀመረበት የጊዜ ማእቀፍ አንፃር የሚጠበቀውን አላማ በሚፈለገው መጠን ማሳካት ካለመቻሉም በላይ፡ ከለላ የተሰጣቸው የንግድ ዘርፎች ሰፊ የአገልግሎት ተደራሽነት፡ የጥራት እና የብቃት ችግሮች የሚታይባቸው በመሆኑ፡ ለህገ-ወጥ ድርጊት የተጋለጡበት ሁኔታም እየተስፋፋ በመምጣቱ፤

እንዲሁም የተከለሉት የንግድ ሥራ ዘርፎች ለፍትሀዊ ውድድር ያልተጋለጡ ከመሆናቸው እና ከቁጥጥር ስርአቱ አተገባበር ውስንነት ጋር በተያያዙ ምክንያቶች የፖሊሲውን አላማ የተገዳደሩ ተጨማሪ ክፍተቶች በመስተዋላቸው፤

ለአገር ውስጥ ባለሃብት የተከለሉ የወጪ፣ የገቢ፣ የጅምላ እና የችርቻሮ ንግድ ኢንቨስትመንት ዘርፎችን የሚመለከተው ሀገራዊ የፖሊሲ እሳቤ በአዲስ ተሻሽሎ - ዘርፎቹ ፍላጎትና አቅሙ ላላቸው የውጭ ባለሀብቶች ደረጃ በደረጃ እንዲከፈቱ በማድረግ የፖሊሲ አፈፃፀሙን በተግባር እየፈተሹ እና በሂደትም ለውጥ እና ጥቅሞችን በመመዘን እያሰፉ የመሄድ አቅጣጫን መከተል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፡

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ በኢንቨስትመንት አዋጁ አንቀጽ 6(4) እና አንቀጽ 31(1)(ሠ) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል ፩
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ መመሪያ “የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ በተከለሉ የወጪ፣ ገቢ፣ ጅምላ እና ችርቻሮ ንግድ ስራዎች የውጭ ባለሀብቶች ኢንቨስትመንት ተሳትፎ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር ፲፪፩/፳፻፲፮ ዓ.ም” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. <u>ትርጓሜ</u>**

*በዚህ መመሪያ፡-*

*፩/ "አዋጅ" ማለት የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፲፩ሺ፹/፪ሺ፲፪ ነው።*

*፪/ "ደንብ" ማለት የኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር ፬፻፸፬/፳፻፲፪ ነው።*

*፫/ "ኮሚሽን" ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፵፭ መሠረት እንደገና የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ነው።*

*፬/ "ቦርድ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፵ መሠረት እንደገና የተቋቋመው የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ቦርድ ነው።*

*፭/ "የውጭ ባለሃብት" በኢንቨስትመንት አዋጁ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል።*

*፮/ "የወጪ ንግድ"፣ "የገቢ ንግድ"፣ "የጅምላ ንግድ" እና "የችርቻሮ ንግድ" በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፱፻፹/፪ሺ፰ (አንደተሻሻለ) የተሰጠው ትርጉም ይኖራቸዋል።*

*፯/ "የቁም እንስሳ" ማለት የጋማ ከብቶች እና የቀንድ ከብቶች ማለት ነው።*

*፰/ "አግባብነት ያለው አካል" ማለት ከዚህ መመሪያ ጋር በሚያያዙ ጉዳዮች ላይ በሌላ ህግ የቁጥጥር፣ ክትትል ወይም ማሳለጥ ሀላፊነት የተሰጠው አካል ነው።*

*፱/ በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ሌሎች ቃላት እና ሐረጎች በአዋጁ እና በደንቡ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።*

**፫. <u>አላማ</u>**

*የመመሪያው አላማ ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች በተከለሉ የወጪ፣ የገቢ፣ የጅምላ እና ችርቻሮ ንግድ ስራዎች የውጭ ባለሀብቶች የሚሳተፉባቸውን መስኮች መዘርዘር፣ ተፈፃሚ የሚሆኑ ቅድመ-ሁኔታዎችን መመስረት፣ እንዲሁም አግባብነት ያላቸው አካላት የሚኖራቸውን የማሳለጥ እና የቁጥጥር ስራ ዝርዝር ማመላከት ነው።*

**፬. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

*ይህ መመሪያ በቦርዱ ውሳኔ መሰረት ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች በተከለሉ የንግድ ዘርፎች የውጭ ባለሀብቶች በሚኖራቸው ተሳትፎ፣ የፈቃዶች ጥያቄ እና ምላሽ አሰጣጥ፣ እና አግባብነት ያላቸው አካላት ተፈፃሚ በሚያደርጉት ማናቸውም አሰራር እና የቁጥጥር ጉዳይ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።*

## ክፍል ፪
## የውጭ ባለሃብቶች ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች በተከለሉ የወጪ፣ የገቢ፣ የጅምላ እና የችርቻሮ ንግድ ኢንቨስትመንቶች የሚሣተፉባቸው ሁኔታዎች

**፭. በ<u>ወጪ ንግድ ስለመሳተፍ</u>**

*፩/ ማንኛውም የውጭ ባለሀብት በጥሬ ቡና፣ ጫት፣ የቅባት እህል፣ ጥራጥሬ፣ ቆዳ እና ሌጦ፣ የደን ውጤቶች፣ ዶሮ እና የቁም እንስሳትን ከገበያ በመግዛት የመላክ የወጪ ንግድ ኢንቨስትመንት መሰማራት ይችላል።*

*፪/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ ፩ መሰረት አግባብነት ያለው አካል ከኢንቨስትመንት እና ንግድ ፈቃዶች አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የሚያሳልፈው የውጭ ባለሀብቶች ተሳትፎ ውሳኔ መርህ አመልካቹ በዘርፉ የተሻለ ልምድ፣ ወይም አቅም ወይም የገበያ ትስስር ያለው መሆኑን የሚያረጋጥ መሆን አለበት።*

**፮. <u>የወጪ ንግድ ተሳትፎ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ቅድመ-ሁኔታዎች</u>**

*በሌሎች ህጎች የተቀመጡ ዝቅተኛ ካፒታልን፣ የብቃት እና ሌሎች ደረጃዎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በአንቀፅ ፭ መሰረት ማመልከቻ የሚያቀርብ ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከማግኘቱ በፊት የሚከተሉትን ቅድመ-ሁኔታዎች የሚያሟላ እና የውል ግዴታ አስቀድሞ ለመግባት ፈቃደኛነቱን የሚገልፅ መሆን አለበት።*

፩/ በጥሬ ቡና ወጪ ንግድ ለመሳተፍ ጥያቄ የሚያቀርብ የውጭ ባለሀብት ባለፉት ሶስት ተከታታይ ዓመታት በአማካይ ቢያንስ 10,000,000 (አስር ሚሊዮን) የአሜሪካ ዶላር የምርቶች ግዥ ከኢትዮጵያ ሲፈጽም የነበረ ሆኖ፣ ፈቃድ በተሰጠው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ቢያንስ የ10,000,000 (አስር ሚሊዮን) የአሜሪካ ዶላር ወጪ ንግድ ለማከናወን የውል ግዴታ መግባት የሚችል፤

፪/ በቅባት እህል ወጪ ንግድ ለመሳተፍ ጥያቄ የሚያቀርብ የውጭ ባለሀብት ባለፉት ሶስት ተከታታይ ዓመታት በአማካይ ቢያንስ 5,000,000 (አምስት ሚሊዮን) የአሜሪካ ዶላር የምርቶች ግዥ ከኢትዮጵያ ሲፈጽም የነበረ ሆኖ፣ ፈቃድ በተሰጠው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ቢያንስ የ5,000,000 (አምስት ሚሊዮን) የአሜሪካ ዶላር ወጪ ንግድ ለማከናወን የውል ግዴታ መግባት የሚችል፤

፫/ በሻይ እና በጥራጥሬ ወጪ ንግድ ለመሳተፍ ጥያቄ የሚያቀርብ የውጭ ባለሀብት ባለፉት ሶስት ተከታታይ ዓመታት በአማካይ ቢያንስ 1,000,000 (አንድ ሚሊዮን) የአሜሪካ ዶላር የምርቶች ግዥ ከኢትዮጵያ ሲፈጽም የነበረ ሆኖ፣ ፈቃድ በተሰጠው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በየዘርፎቹ ቢያንስ የ1,000,000 (አንድ ሚሊዮን) የአሜሪካ ዶላር ወጪ ንግድ ለማከናወን የውል ግዴታ መግባት የሚችል፤

፬/ በቆዳ እና ሌጦ፣ ደን ውጤቶች፣ እና ዶሮ በመላክ የወጪ ንግድ ለመሳተፍ ጥያቄ የሚያቀርብ የውጭ ባለሃብትን በተመለከተ በምርቶቹ ያለፉት ሦስት ዓመታት አማካይ አፈፃፀሙ ቢያንስ 500,000 (አምስት መቶ ሺህ መቶ ሺህ) የአሜሪካ ዶላር ሆኖ፣ ፈቃድ በተሰጠው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በየዘርፎቹ ቢያንስ የ500,000 (አምስት መቶ ሺህ መቶ ሺህ) የአሜሪካ ዶላር ወጪ ንግድ ለማከናወን የውል ግዴታ መግባት የሚችል፤

፭/ የቁም እንስሳትን በመላክ የወጪ ንግድ ለመሳተፍ ጥያቄ የሚያቀርብ የውጭ ባለሃብትን በተመለከተ የቀደመ አፈጻጸም እና ፈቃድ ከተሰጠ በኋላ የሚጠበቅ የክንውን የውል ግዴታ አይኖርም፤

፮/ የቀደመ የግዥ ታሪክ የሌለው የውጭ ባለሃብት ከሆነ በወጪ ንግድ ለመሳተፍ በቅድሚያ የተረጋገጠ ገበያ ያለው ሆኖ ለጥሬ ቡና ቢያንስ የ12,500,000 (አስራ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ) የአሜሪካ ዶላር፣ ለቅባት እህል ቢያንስ የ7,500,000 (ሰባት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ) የአሜሪካ ዶላር፣ ለሻይ እና ጥራጥሬ ቢያንስ 1,500,000 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ) የአሜሪካ ዶላር፣ በቆዳ እና ሌጦ፣ ደን ውጤቶች፣ እና ዶሮ የ750,000 (ሰባት መቶ ሃምሳ ሺህ) የአሜሪካ ዶላር የግዥ ውል ስምምነት ማቅረብ የሚችል፤

፯/ የቀደመ የግዥ ታሪክ የሌለው የውጭ ባለሃብት ሆኖ በዚህ መመሪያ የተሸፈኑ ሌሎች የወጪ ንግድ ምርቶችን በተመለከተ በቅድሚያ የተረጋገጠ ገበያ ያለው እና በአመት ቢያንስ የ500,000 (አምስት መቶ ሺህ) የአሜሪካ ዶላር የግዥ ውል ስምምነት ማቅረብ የሚችል፤

፰/ ባለሀብቱ በኢትዮጵያ የሚገኝ ጥሬ ዕቃን በመጠቀም ያለቀለት ምርት ሲያመርት የቆየ በውጭ የሚገኝ አምራች ድርጅት ከሆነ፣ ወይም የውጭ አምራች ድርጅት ሆኖ ከኢትዮጵያ የተገዛ ጥሬ እቃን በመጠቀም እና ይህን በመግለፅ ለገበያ ማቅረብ የሚችል ከሆነ እና ለዚህ በቂ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል።

**፯. <u>የወጪ ንግድ ኢንቨስትመንት ፈቃድ እድሳት ወይም መሰረዝ</u>**

፩/ በዚህ መመሪያ መሰረት በወጭ ንግድ ስራ የሚሳተፍ የውጭ ባለሀብት በውል የገባውን የኢንቨስትመንት ፈቃድ ቅድመ-ሁኔታዎችን የማክበር ግዴታ አለበት።

፪/ የኢንቨስትመንት ወይም የንግድ ስራ ፈቃድ የሚታደሰው ባለሀብቱ የገባውን ግዴታ በአግባቡ ስለመፈጸሙ አግባብነት ባላቸው አካላት ክትትል ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

፫/ የኢንቨስትመንት ወይም የንግድ ስራ ፈቃድ አለመታደስ፣ መታገድ ወይም መሰረዝ በፈቃዶቹ ላይ የተመሰረቱ መብቶች እና ጥቅሞች መታገድ ወይም መሰረዝን ያስከትላል።

**፰. <u>በገቢ ንግድ ስለመሳተፍ</u>**

፩/ ከማዳበሪያ እና ነዳጅ ገቢ ንግድ በስተቀር ማንኛውም የውጭ ባለሀብት በደንቡ ለአገር ውስጥ ባለሃብት በተከለሉ በሁሉም የገቢ ንግድ ኢንቨስትመንት መስኮች መሰማራት ይችላል።

፪/ አግባብነት ያለው አካል ከኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የሚያሳልፈው የውጭ ባለሀብቶች ተሳትፎ ውሳኔ መርህ አመልካቹ በዘርፉ የተሻለ ልምድ፣ ወይም አቅም ወይም የገበያ ትስስር ያለው መሆኑን የሚያረጋጥ መሆን አለበት።

፱. <u>የገቢ ንግድ ተሳትፎ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ቅድመ-ሁኔታዎች</u>

በሌሎች ህጎች የተቀመጡ አነስተኛ ካፒታልን፣ የብቃት ደረጃዎችን፣ እንዲሁም ለውጭ ባለሀብቶች የተፈቀዱ የገቢ ንግድ ሥራዎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በአንቀፅ ፰ መሰረት ማመልከቻ የሚያቀርብ ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከማግኘቱ በፊት እንደአግባብነቱ የሚከተሉትን ቅድመ-ሁኔታዎች የሚያሟላ ወይም ቁመና ያለው መሆን አለበት።

፩/ በገቢ ንግድ ስራ የሚያስመጣው ምርት ራሱ አምራች መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል ባለሀብት፣ ወይም

፪/ የአምራች ወኪል የሆነና ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፤ ወይም

፫/ ቀደም ሲል በአገራችን ኢንቨስትመንት ተሣትፎ በማድረግ 50% እና ከዚያ በላይ የሚሆን ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ነባር የውጭ ባለሃብት፤ ወይም

፬/ አምራች ወይም የአምራች ወኪል ያልሆነ የውጭ ባለሀብት ቢያንስ 10,000,000 (አስር ሚሊዮን) የአሜሪካ ዶላር ዋጋ ግምት ያለው ገቢ እቃ በየአመቱ ለማስመጣት በዝርዝር የተዘጋጀ ዕቅድ ማቅረብ የሚችል ሆኖ አግባብነት ካለው ፈቃድ ሰጪ አካል ጋር የውል ስምምነት የሚገባ፤

፲. <u>የገቢ ንግድ ኢንቨስትመንት ፈቃድ እድሳት ወይም መሰረዝ</u>

፩/ በአንቀፅ ፱ ንኡስ አንቀፅ (፬) መሰረት በገቢ ንግድ ስራ የሚሳተፍ የውጭ ባለሀብት በውል የገባውን የኢንቨስትመንት ፈቃድ ቅድመ-ሁኔታዎችን የማክበር ግዴታ አለበት።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (፩) መሰረት በገቢ ንግድ ለመሰማራት የተሰጠ የኢንቨስትመንት ወይም የንግድ ስራ ፈቃድ የሚታደሰው ባለሀብቱ የገባውን ግዴታ ስለመፈጸሙ አግባብነት ባላቸው አካላት ክትትል ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

፫/ የኢንቨስትመንት ወይም የንግድ ስራ ፈቃድ አለመታደስ፣ መታገድ ወይም መሰረዝ በፈቃዶቹ ላይ የተመሰረቱ መብቶች እና ጥቅሞች መታገድ ወይም መሰረዝን ያስከትላል።

፲፩. <u>በጅምላ ንግድ ስለመሳተፍ እና የኢንቨስትመንት ፈቃድ ቅድመ-ሁኔታዎች</u>

፩/ ከማዳበሪያ ጅምላ ንግድ በስተቀር ማንኛውም የውጭ ባለሀብት በደንቡ ለአገር ውስጥ ባለሃብት በተከለሉ ሁሉም የጅምላ ንግድ ኢንቨስትመንት መስኮች መሰማራት ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ ፩ መሰረት ፈቃድ የሚሰጠው ባለሀብት በአስመጪነት ፈቃድ ከውጭ ያመጣው ምርትን ጨምሮ ከአገር ውስጥ አምራቾች የገዛውን ምርት በጅምላ ንግድ መሸጥ ይችላል።

፫/ በሌሎች ህጎች የተቀመጡ አነስተኛ ካፒታል፣ የብቃት ደረጃዎችን የሚመለከቱ እንዲሁም ለውጭ ባለሀብቶች የተፈቀዱ የጅምላ ንግድ ሥራዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በዚህ መመሪያ መሰረት ማመልከቻ የሚያቀርብ ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከማግኘቱ በፊት፣

ሀ/ ዝርዝር የውል ግዴታ አስቀድሞ ለመግባት ፈቃደኛነቱን በፅሁፍ የገለፀ፣ እና

ለ/ የጅምላ ስራዎቹን ለማሳለጥ የሚያግዝ ዘመናዊ የግብይት አውታር ለመገንባትና የተሳለጠ የሎጂስቲክስ አገልግሎት ለማቅረብ ግዴታ የሚገባ መሆን አለበት።

፬/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (፫)(ለ) መሰረት እንዲሟላ የሚጠበቀው አነስተኛ የጅምላ ንግድ የግብይት አውታር ደረጃ የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በሚያወጣው ማንዋል ይወሰናል።

**፲፪. በ<u>ችርቻሮ ንግድ ስለመሳተፍ</u>**

በዚህ መመሪያ መሰረት ማንኛውም የውጭ ባለሀብት በደንቡ ላይ ለአገር ውስጥ ባለሃብት በተከለሉ የችርቻሮ ንግድ ኢንቨስትመንት መስኮች መሰማራት ይችላል።

**፲፫. <u>የችርቻሮ ንግድ ኢንቨስትመንት ፈቃድ ቅድመ-ሁኔታዎች</u>**

፩/ በሌሎች ህጎች የተቀመጡ አነስተኛ ካፒታል፣ የብቃት ደረጃዎችን የሚመለከቱ፣ እንዲሁም ለውጭ ባለሀብቶች የተፈቀዱ የችርቻሮ ንግድ ሥራዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በዚህ አንቀፅ መሰረት ማመልከቻ የሚያቀርብ ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሚያገኘው በሚከተሉት ሁኔታዎች መሰረት ብቻ ነው።

ሀ/ የችርቻሮ ንግድ ስራው ቢያንስ 2000 ካሬ ሜትር ስፋት ባለው መሬት ወይም የመሸጫ ህንጻ ወለል ላይ የሚያርፍና በአንድ ባለሃብት ባለቤትነት የሚደራጅ ሆኖ በሦስት አመት ጊዜ ውስጥ አምስት በዚህ ደረጃ የሚቋቋሙ ሱፐር-ማርኬቶችን የሚከፍት ከሆነ እና የንግድ ፈቃድ ለማግኘት ቢያንስ ሁለቱን አስቀድሞ የሚያጠናቅቅ፣ ለዚህም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከመውሰዱ በፊት ዝርዝር የውል ግዴታ የሚገባ ከሆነ፤ ወይም

ለ/ የችርቻሮ ንግድ ስራው ቢያንስ 5000 ካሬ ሜትር ስፋት ባለው መሬት ወይም የመሸጫ ህንጻ ወለል ላይ የሚያርፍና በአንድ ባለሃብት ባለቤትነት የሚደራጅ ሆኖ፣ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሁለት ሀይፐር ማርኬቶችን የሚከፍት ከሆነ እና የንግድ ስራ ፈቃድ ለማግኘት ቢያንስ አንዱን አስቀድሞ የሚያጠናቅቅ፣ ለዚህም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከመውሰዱ በፊት ዝርዝር የውል ግዴታ የሚገባ ከሆነ፤ ወይም

ሐ/ የችርቻሮ ንግድ ስራው ቢያንስ 10000 ካሬ ሜትር ስፋት ባለው መሬት ወይም የመሸጫ ህንጻ ወለል ላይ የሚያርፍና በአንድ ባለሃብት ባለቤትነት የሚደራጅ አንድ ሞል ለመክፈት የሚችል ከሆነ እና የንግድ ስራ ፈቃድ ለማግኘት ግንባታውን ለማጠናቀቅ ዝርዝር የውል ግዴታ የሚገባ ከሆነ፣

፪/ በንግድ ስራ ፈቃድ መስጫ መደብ መመሪያ ቁጥር 17/2011 ላይ ለሱፐር ማርኬት፣ ለሀይፐር ማርኬት እና ሞል የተሰጡ ትርጉሞች በዚህ አንቀፅ ከተመለከቱ የችርቻሮ ንግድ ማካሄጃ መሰረተ-ልማት ስያሜዎች ጋር የማጣጣም ስራ የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ያከናውናል።

፫/ የውጭ ባለሀብቶች በዝቅተኛ ካፒታል እና አነስተኛ የወለል መጠን - መልካም ስም ባላቸው ነጠላ ምርቶች ችርቻሮ ስራ ላይ የሚሰማሩበትን ሁኔታ ቦርዱ በጉዳይ ላይ እየተመሰረተ ውሳኔ ያሳልፋል።

## ክፍል ፫

## የተቋማት የቁጥጥር እና የክትትል ስርአት

**፲፬. <u>የተቋማት ሀላፊነት</u>**

፩/ አግባብነት ያላቸው ሁሉም አካላት ይህን መመሪያ ለማስፈፀም የሚያስችሉ ዝርዝር ተቋማዊ ስርአት ይዘረጋሉ።

፪/ በዚህ መመሪያ መሰረት የወጪ ምርት የሚከታተሉ አግባብነት ያላቸው አካላት ከወጪ ንግድ ምርቶች ጋር በተያያዘ ግልፅ፣ ምቹ፣ ዘመናዊ እና ፍትሃዊ የመወዳደር ሁኔታዎችን የሚፈጥር የሀገር ውስጥ ግብይት ስርአት የመገንባት፣ እንዲሁም የወጪ ምርቶች ወቅታዊ የመዳረሻ ሀገራት የገበያ ዋጋ ዳሰሳ እና የመረጃ ስርአት የማደራጀት እና እንዳስፈላጊነቱ በዚህ ላይ የተመሰረተ ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ የመተግበር፤ እና የቅድመ እና ድህረ-ሺያጭ የቁጥጥር ስራዎችን የሚመለከቱ አሰራሮችን የመመስረት እና የማጠናከር ኃላፊነት አለባቸው።

፫/ የገቢ እቃዎች ንግድን ከመክፈት ጋር በተያያዘ አግባብነት ያለው አካል በገቢ ንግድ ላይ በሚጣል ቀረጥና ታክስ አመዳደብ እና አሰባሰብ ረገድ ያለውን አሠራር የማጠናከር እና የተሳለጠ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት።

፬/ የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በዚህ መመሪያ መሰረት የሚሳለጥ የጅምላ እና የችርቻሮ ንግድን በተመለከተ በገበያ ስርአቱ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ፀረ-ውድድር ተግባራትን ለመቆጣጠር እና የሸማቾችን መብት ለማስከበር የሚያስችል ጠንካራ አደረጃጀትና አሠራር ይፈጥራል።

፭/ ኮሚሽኑ የውጭ ባለሀብቶችን ማመልከቻ ይቀበላል፤ ተጠባቂ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ይመረምራል፤ አግባብነት ያላቸው ሂደቶችን በመከተል የንግድ ምዝገባ ያከናውናል፤ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት እና የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፤ የአፈፃፀም ውል ግዴታዎችን አዘጋጅቶ ይፈራረማል፤ አፈፃፀሙን ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር በመሆን ይከታተላል።

፮/ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የኢንቨስትመንት ፈቃድ ላገኙ የውጭ ባለሀብቶች የንግድ ስራ ፈቃድ ይሰጣል፤ የንግድ ስራ ሂደቶችን ይቆጣጠራል።

፯/ በዚህ መመሪያ ማእቀፍ ተግባራዊ የሚደረጉ ስራዎች የተፈለገውን አላማ እያሳኩ መሆኑን ለመመዘን እና ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ እንዲቻል የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የግብርና ሚኒስቴር፣ የጉምሩክ ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና ሌሎች በቦርዱ የሚሰየሙ አካላት አንድ ቋሚ የጋራ ኮሚቴ ያደራጃሉ። አፈፃፀሙን ይከታተላሉ። የቋሚ የጋራ ኮሚቴው ሰብሳቢ በቦርዱ ይሰየማል።

**ክፍል ፬**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

፲፭. <u>የመተግበር ግዴታ</u>

፩/ በዚህ መመሪያ የተሸፈነ ጉዳይ የሚመለከተው ማንኛውም የፌዴራል መንግሥት አካል መመሪያውን የማክበር እና የመፈጸም ግዴታ አለበት።

፪/ ማንኛውም ሰው ወይም አካል ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት።

፲፮. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር እና በኮሚሽኑ ድህረ-ገፅ ላይ ከተጫነበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**ዓብይ አህመድ ዓሊ (ዶ/ር)**

**የኢትየጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ ሰብሳቢ**